# የአውሬው ቁጥር 666

“የአውሬው ምስል ሊናገር እንኳ ለአውሬውም ምስል የማይሰግዱለትን ሁሉ ሊያስገድላቸው፥ ለአውሬው ምስል ትንፋሽ እንዲሰጠው ተሰጠው። ታናናሾችና ታላላቆችም ባለ ጠጋዎችና ድሆችም ጌታዎችና ባሪያዎችም ሁሉ በቀኝ እጃቸው ወይም በግምባራቸው ምልክትን እንዲቀበሉ፥

የአውሬውም ስም ወይም የስሙ ቍጥር ያለው ምልክት የሌለበት ማንም ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንዳይችል ያደርጋል። ጥበብ በዚህ አለ። አእምሮ ያለው የአውሬውን ቍጥር ይቍጠረው፤ ቍጥሩ የሰው ቍጥር ነውና፥ ቍጥሩም ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት ነው። *(ራዕ.13:15-18)*




666! የአውሬው ቁጥር እንደሆነና በመጨረሻው ዘመን አንድ ጉዳይ የሚሰራበት ቁጥር እንደሆነ የማያውቅ ሰው በምድር ላይ ብዙ ላይሆን ይችላል። አሁን ያለንበት ዘመን ከየትኞቹም ዘመናት ይልቅ በወረቀት በወይንም በብረት በተሰራ ገንዘብ የሚነግድበት ዘመን እየቀየረ በቁጥር የሚሰራበት ዘመን ላይ ደርሰናል። ህዝብም ጥሬ ገንዘብ አልባ "cashless" እየሆነ ነው። ይህ ማለት ገንዘብ ከማግኘት ማጣት ማለት ሳይሆን በገንዘብ ከመገበያየት ይልቅ በክሬዲት ካርድ መጠቀምን እያዘወተረ ነው። አበዳሪዎችም በብዙ ማባበል ከ18 አመት በላይ የሆነን ሰው ሁሉ ክሬዲት ካርድ በመስጠት “የዱባ ጥጋብ ያለስንቅ ያዘመታል” እንዲባል ሰዎች በሌላቸው ገንዘብ የማያስፈልጋቸውን ሁሉ በእዳ እየገዙ ከአቅማቸው በላይ በእዳ እንዲዘፈቁ እየሆነ ነው፡፤

የንግድ ሱቆች፣የገበያ አዳራሾች፣ ምግብ ቤቶች፣ሆቴሎችም፣የአየር መንገዶች፣ወዘተ. በብድር ካርድ መገበያየት ስራቸውን የቀለጠፈ እንዲሆን አድርጎላቸዋል። እቃ ከተገዛ በኋላ የብድር ካርዱ በሱቁ ውስጥ ባለው ካርዱን ማንበቢያ ውስጥ ያልፍና ገንዘብ ወዲያውኑ ከባንኩ ወደ እቃው ወደ ተገዛበት ሱቅ ይዘዋወራል። ምንም የወረቀት ገንዘብ ሳይወጣ በአጭር ሰኮንዶች ውስት በቀላሉ ሰው መገበያየት ቻለ ማለት ነው።

የብድር ካርዶች በአለም ሃገሮች ሁሉ ተሰራጭተዋል። በተመሳሳዩ "IC Card" ወይንም "Smart Card" ተብሎ የሚጠራው የብድር ካርድ ደግሞ በላዩ ላይ የኮምፒውተር መረጃ መያዣ (computer chip) አለበት። በዚህ በመረጃ መያዣውስጥ በተለይም በምዕራቡ አለም አስፈላጊ የሆኑት የባንክ ምስጢር ቁጥሮች፣ የፓስፖርት ቁጥር፣ የህክም ሰነዶችና የመንጃ ፈቃድ ቁጥሮች ከነፎቶግራፍ ወዘተ. አብረው በስውር ተሰርተዋል (embedded)።



መንግስታት በዜጎቻቸው መካከል የሚሆነው የቁማርና የአደገና ዕጽ ንግድ ለመቆጣጠር የሚያስችላቸውን ይህንን ህዝብን ገንዘብ አልባ በሆነ መንገድ በመቆጣጠር ሰላም ለማስፈን ሲሉ ይህን አሰራር ቶሎ ተቀብለውታል። በተጨማሪም መታወቂያ ደብተሮች እንደቀድሞው ዘመን በወረቀትና በማህተም ብቻ የሚታወቁ አይደሉም። በቀላሉ በዘመናዊ ፎቶ ኮፒ ማንሻዎች ብዙ ወንጀሎች እየተሰሩ ስለሆነ ስህተት አልባና ማንም በማጭበርበር እንዳይጠቀምበት የመታወቂያ ወረቀቶች፣ ፓስፖርቶች፣ የመንጃ ፈቃዶች ወዘተ. በእጅ አሻራ ማንበቢያ ብቻ እንዲነበቡ ተደርገው በውስጣቸው ምስጢራዊ መረጃዎች ይቀመጡባቸዋል።



"Smart Card" ያልናቸውም በመሰረቅ ወይንም በተለያየ መንገድ በጎ ላልሆነ ነገር ሌሎች ሰዎች ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ስለዚህ "Smart Card" አሁን በአይን በማይታይ (micro-chips) ተሰርቶ በቤት እንሰሶች ጆሮ ላይ እየተመታ ነው። በ2012 መጨረሻ ገደማ በአሜሪካን ምክር ቤት ለህክምና ኢንሹራንስ መቆጣጠሪያ ያስፈልጋል በሚል ሰበብ በፕሪዝዴንት ኦባማ አነሳሽነት በሰዎች ቀኝ እጅ ላይ እስከ ሜይ 23፤2013 ድረስ በዜጎች ላይ እንዲደረግ ተወስኗል።



ይህ RFID (Radio Frequency Identifcation) በመባል የሚታወቀው (micro-chips) በሰው ቀኝ እጅ ላይ የሚቀበረው መሳሪያ የስንዴ ቅንጣት ይዘቱ የሚያኽል ነው። በዚህም አሜሪካ የአውሬውን ምስል በመስራት መንገድ በመጥረግ ላይ ትገኛለች። ያለማንበቢያ መሳሪያው በሰው እጅ ውስጥ የተቀበረው ይህ (micro-chips) የት እንዳለ አይታወቅም። እስከቅርብ ጊዜ ድረስ በቤት እንሰሶች ጆሮ ላይ እየተመታ የነበረው (micro-chips) አሁን በሰዎች እጅ ላይ መደረጉ ገሃድ እየሆነ መጥቷል። ይህንንም ሃዋርያው ዮሃንስ በራዕዩ ላይ አመልክቶናል።



በዚህ በmicro-chips ውስጥ የሰውን ሁለንተናዊ ጤና መረጃ የሚሰበስብና ምናልባት በላዩ የተመታበትም ሰው ሳያውቀው በጤናው ውስጥ ችግር ከመነሳቱ ቀደም ብሎ መሳሪያው ወደ ኀኪሙ ኢሜይል ወይንም ስልክ ሊደውልና ማንም በምን በሽታ ውስጥ እንዳለ ቀድሞ መረጃ ሊልክ ይችላል። ከክሬዲት ካርድ በበለጠ ስለሚያስገኘው ጥቅም ሲባል ብዙዎች እንደሚቀበሉት ምንም አያጠራጥርም።

በውትድርናውም አለም አገሮች በሳተላይት ወታደሮቻቸው የት እንዳሉ ለማወቅ በእጆቻቸው ላይ እንዲመታ እያደረጉ ነው። ሰዎች ከአገር አገር ሲሄዱ መታወቂያ ወረቀት ሳይሆን እጃቸውን ወይንም ግንባራቸው ብቻ በመሳሪያ አስነብበው (scan)

ማንኛውንም ኬላ አልፈው ይጓዛሉ። የመሳሪያው ጥቅም ጎልቶ በቅስቀሳ ሲነገር ሰው ሁሉ ሊመታ ይሄዳል፤ እውነቱ ግን ለጸረ ክርስቶስ አለምን ለመቆጣጠር እጅግ ቀሊል ያደርግለታል።

አዲሱ የአለም ስርዓት "New World Order" ተብሎ በየስፍራው የታወጀለት ስርዓት እግዚአብሔርን አውጥቶ አለምን “ዲሞክራሲ” በሚል እውነተኛ ባልሆነ ፖለቲካዊ መርኅ ለጸረ ክርስቶስ ለማዘጋጀት የሰይጣን ዘመናዊ እቅድ ነው። እንግዲህ በአዲሱ የአለም ስርዓት ለመገበያየት የአለም ህዝብ ሁሉ በኮምፒውተር መዝገብ ውስጥ ቁጥር ይሰጠዋል። በድረ ገጽ መግቢያ ላይ w.w.w. = world wide web = ፯..፯.፯ በዕብራይስጥ (ቫቭ.ቫቭ.ቫቭ) ይባላል። የዚህም ቃል የቀመር መለኪያው 6 ቁጥር ነው፤ ስለዚህም w.w.w. የሚለው የድረ ገጽ 666 ማለት ይሆናል። በዘመናችም ሰው ሁሉ የመንጃ ፈቃድ ቁጥር፣የካርድ ቁጥር፣የመኖሪያ ፈቃድ ቁጥር...ወዘተ. በሚል የቁጥር ተራ የተመዘገበ ስለሆነ የጸረ ክርስቶስ አሰራር የተመቻቸና የተጠረገ መንገድ እንደተበጀለት እንመለከታለን፤ ሰውም በዚያ ቁጥር ይገዛል ይለውጣል። ከ2000 አመታት በፊት ዮሃንስ ይህንኑ ክስተት በራዕ.14፡9-10 እንዲህ ብሎ ተንብዮታል!

*"ሦስተኛም መልአክ ተከተላቸው፥ በታላቅ ድምፅ እንዲህ አያለ። ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግድ በግምባሩም ወይም በእጁ ምልክቱን የሚቀበል ማንም ቢኖር፥10 እርሱ ደግሞ በቍጣው ጽዋ ሳይቀላቀል ከተዘጋጀው ከእግዚአብሔር ቍጣ ወይን ጠጅ ይጠጣል፥ በቅዱሳንም መላእክትና በበጉ ፊት በእሳትና በዲን ይሳቀያል።..." (ራዕ.14:9-10)*

የአውሬውን ቁጥር መውሰድ ገበያ ለማድረግ የሚደረግ የኢኮኖሚ ውስኔ ብቻ ሳይሆን እንደ ዮሃንስ ትንቢት ከሰይጣን ጋር የሚገባ ኪዳን፣ሰይጣናዊ አምልኮና ጸረ ክርስቶስን የህይወት መሪ አድርጎ መቀበል እንደማለት ነው። ይህንን ቁጥር የሚወስድ ሰው በምንም አይነት ምህረትና ይቅርታን ከእግዚአብሔር ለዘላለም አያገኝም፤መጨረሻውም ገሃነም እሳት ይሆናል።